# ለምድ በደበሎ ?!

*አሥራደው (ከፈረንሳይ)*

*በመስቀል ላይ ሳይሆን በብዕር ላይ ለወገኖቹ ፍቅር ተቸንክሮ የነፍሱን ጥሪ ሲያስተናግድ ሕይወቱ ያለፈው ደራሲ በዓሉ ግርማ፤ በሆዱ ውስጥ ጩሩርር እያለ የሚጮኸውን ወስፋት እያዳመጠ ሲያስተናግድ ከነበረውና **ቅንቡርስ :ቅንቡርስ** ከሚሸተው ተስፋዬ ገብረ አብ ጋር በማነጻጸር **« የሚገማሸረው ብእር »** በሚል ርዕስ በአቶ **ያገር ልጅ** የቀረበውን ጽሑፍ አንብቤ ልቤ በመድማቱና የአይምሮዬ መረዋ እያቃጨለ ሰላም ስለነሳኝ ነው ይችን ማስታወሻ መጨንቆር የተገደድኩት ::*

*በነገራችን ላይ ሰዎችን በድርጊታቸው እንጂ በሰብዕናቸው ላይ ነቀፋም ሆነ ጥላቻ የለኝም፤ በዓሉ ግርማም ያስተማረኝ ፍቅርን እንጂ ጥላቻን ስላልሆነ በተስፋዬ ገብረ አብ ላይ ምንም ዓይነት የሰብዕና ጥላቻ የለኝም ::*

*ወገኖቼ ! ተስፋዬ ገብረ አብ የሚጽፈው ወይም እየጻፈ ያለው ኑዛዜውን ነው፤ ከወያኔ ጋር ሆኖ የሠራው ሃጥያቱ እያሳደደው ነብሱ የሲቃ ጩኸቷን ስትጮህ የሥጋው ክብደት ከመሬት ስበት በበለጠ ወደታች እየጎተተው እንጥሮጦስ የወረደ የቁም ሟች የሚያቃትተው የመጨረሻ እስትንፋስ !*

*በዓሉ ግርማ ግን ትንቢት ነው፤ ዛሬ ላይ ቆመን : ነገንና ተነገ ወዲያን ወገግ ብሎ እንድናየው ጨራውን የሚፈነጠቅ **የማለዳ ፀሐይ !!***

*ወንድሜ አቶ **ያገር ልጅ** ባንድ ቃል **« መገማሸር »** በምትለዋ በቁማቸው ተፈተው አገር አስረክበዋል፤ ከቃላት በስተጀርባ የተሰፍዬን የትውልድ አቀራራጭ ምግባር በዐይነ ሕሊናቸው የዳሰሱት አይመስለኝም፤ ተስፋዬ ጥንብ: ጥንብ : የሚሸት ሥራውን የቃላት ሽቶ ቢያርከፈክፍበትም ክርፋት ክርፋት መተንፈጉን አይተውም « ለአፈ ግም ድፍን አፍንጫ ያዝለታል » ካልሆነ በስተቀር ::*

*በቃላት አመራረጥ በኩልም ቢሆን: በዓሉ ግርማ እንደ ተስፋዬ « የድንቢጥ ወፍ የመሳሰሉትን» ሳይሆን: እንደ ተራራ የገዘፉ፤ እንደአልማዝ ያሸበረቁ፤ እንደ ፀሐይ ልብን አሙቀው: እንደ ውሃ ጥምን በመቁረጥ: ሥጋን አዝናንተው: ነፍስን በሰረገላ እሹሩሩ እያሉ: ወደ ሰማየ ሰማያት የሚያመጥቁ: ቃላትን ነው የሚጠቀመው ::*
*የርሶን ለርሶ ልተወውና እኔ ተስፋዬ በሚጽፍበት የፈርስ ብዕር ጨዳራ ጨዳራ መሽተት አልሻም :: ተስፋዬ ሆዱ አሸንፎት በሸንፍላው እያሰበ የሠራውን ሥራ ዛሬ እንደ ገድል ቢያቀርብ ዲሪቶ ደራቾች ይዋቡበት እንደሁ እንጂ እንደ እኔ በጥበብ ኩታ መዋብ ለለመዱ አይስማማም ::*

« በዓሉ በረዥም ልቦለድ፤ ተስፋዬ ደግሞ ፡ በታሪካዊ ልቦለድና ፡ በኢልቦለድ፤ ሥራዎቻቸው...... ባንድ ጎራ ያሰልፋቸዋል » ይሉናል ወንድማችን ያገር ልጅ፤

ውድ ወንድሜ ያገር ልጅ ! በዓሉ ግርማን በወጉ የሚያውቁት አይመስለኝም፤ በዓሉ ግርማን ለማወቅ ደግሞ የግድ በአካል ማግኘት የሚያሻ አይመስለኝም፤ በዓሉ በሥራዎቹ የሚገለጽ ፍንትው ያለ የቀትር ፀሐይ ነው፤ ጨለማ ለብሶ ሲንጎዳጎድ አያገኙትም ::

በዓሉ ግርማ ሃቅ ነው በውሸት ሰብዕናውን ሳያጎድፍ ሳመነበት ቆሞ ሳመነበት ሕይወቱን የሰጠ ::

በዓሉ ግርማ ቃል (ትንቢት) ነው ፡ ከአድማስ አድማስ እየተሸጋገረ ገና በማለዳ በጧቱ የአገራችን የኢትዮጵያ ዕጣ እንዳሳማረው ሲነግረን ጆሯችንን ደፍነን አልሰማም ያልነው ነብይ ::

በዓሉ ግርማ ጀግና ነው፤ በብዕር መትረየሱ ጠላትን የሚማርክ፤ ግን በድሉ የማይኩራራ ለተሸናፊም የሚገባውን ክብር የማይነፍግ ሰው አክባሪ :: « ኦሮማይን ይጠቅሷል »

በዓሉ ግርማ ውበት ነው: ከሰብዕናው ጀምሮ የቃላት አመራረጡ፤ የዐረፍተ ነገር ድርደራው፤ የገጸ ባሕሪያት ፈጠራው፤ የሚያነሳው፤ የሚጥለው፤ የሚወረውረው በሙሉ በውበት የተሞላ ነው :: ጠይም ጣኦት ሉሊትን ይጠቅሷል፤ « ከአድማስ ባሻገር »

እናም በዓሉ ግርማ የምናመልከው የብዕር ጣዖታችን ነው ::

በዓሉ ግርማ ፍቅር ነው፤ እንደ ክቡር ሐዲስ ዓለማሁ (ለሳቸው ያለኝ ክብርና አድናቆት እንደተጠበቀ ሆኖ) « እሷ በሱ፤ እሱ በሷ ውስጥ ተያይዘው ጠፉ » በማለት ማጨማጨም ብቻ ሳይሆን: በሁለቱ ፍጡራን ገላ ሰበቃን ፈጥሮ የወሲብ ጧፍ የሚያንቦገቡግ ::

በዓሉ ግርማ መሰላል ነው ፡ ሕልምን ከዕውነታ የሚያሳስም ፡ « የሕሊና ደወልን » አንብበውት ከሆነ ትምህርት ቤቱ ተሠርቶ ሲያልቅ « ደውይው ! የሱጴ ቦሮ ሕዝብ ይስማው! ሲላትና እሷም ደወሉን ኳ!ኳ !ኳ !....... ስታደርገው» ልብ ይነዝራል ልብ ላለው ::

በዓሉ ፈጠራ ነው ፡ « ከሱ ይልቅ የብብቱና የጫማው ሽታ ቀድሞ ቢሮ የሚገባ፤ መጥረኒያ ፊቱን....፤ ሲራመድ እንደኳስ ይነጥራል፤ ድቡልቡል የሆነ ፊቱን.....፤ እናቴ ትሙት ማለትን የሚያበዛ.....፤ ሲጃራ መግዛት የማይሆንለትና: ክብሪት ይዞ ከቢሮ ቢሮ እየዞረ ሲጃራ የሚቃርመውን....ኧረ ስንቱ !! እያለ የሚፈጥራቸውን ገጸ ባሕሪያትና የውብ ቃላት ድርደራውን ለመኮምኮም « ከአድማስ ባሻገርን » ይገላምጡ ::

በመጨረሻም በዓሉ ግርማ ሰው ነው፤ የብዕሩን ሕብስት አብልቶ ሳያጠግበን፤ የሰነ ጽሑፍ ጥማችንን ሳይቆርጥ፤ በሃገር ፍቅር ነብሳችንን እንዳሰጨነቀና ስጋችንን እንደቦጨቀ፤ ሕይወቱ በጨካኞች የጥበብና የስነጽሁፍ አጋሚዶዎች ተቀጠፈ ። እናም ዛሬ በደምና በዕንባ በተቀላቀለ ብዕር በመጻፍ ልንዘክረው እንገደዳለን ።

ለኔ ተስፋዬ ገብረ አብ፡ በድርጊቱ እንደ መርገም ጨርቅ ቢያጥቡት የማይጠራ ሲሆን፤ በዓሉ ግርማ ግን፡ ለኔና ለመሰሎቼ የክት ልብሰ ኩታችን ነው፤ ቱር ብለን እናሸበርቅበታለን፤ እንደምቅበታለን፤ ልባችንም እንደ ሠንጋ ፈረሰ በደስታ ደንገላሳ ይጨፍራል።

ለውድ ወንድሜ የአገር ልጅ! ለምድ በደበሎ አይለወጥምና፡ በዓሉን ከተስፋዬ ማነጻጸር አልማዝን በመዳብ፡ለመለወጥ እንደመሻት ሆነብኝና አልዋጥልህ አለኝ፤ በዚህ እርሰዎም ሆኑ ተስፋዬ ቂም እንደማትቋጥሩብኝ ተስፋ አለኝ። ቂም የደካሞች በትር ነው፡ለብዕር መልሱ ብዕር እንጂ፡ጥይት ወይም መትረየስ መሆን የለበትምና! ከአክብሮት ጋር ።

ተስፋዬስ ምን ይል ይሆን? በርግጥ ከበዓሉ ግርማ ጋር በዕኩል እነፃጸራለሁ ይለን ይሆን? እስቲ ከራሱ አንደበት እንስማ!

በዓሉ ግርማ ከውድ ባለቤቱና ልጆቹ ጊዜውንና ፍቅሩን እየሰረቀ፤ ለሚያከብረውና ለሚወደው የኢትዮጵያ ሕዝብ የለገሰ፤ በመጨረሻም ሕይወቱን በብዕር ጧፍ በማንደድ፤ ለተተኪው ትውልድ የብርሃን ጮራ ፈንጥቆ ያለፈ ድንቅ ደራሲ ነው ።

ከበዓሉ ግርማ ባላነሰ፤ ባለቤቱ ወይዘሮ አልማዝና ልጆቹ፤ በዓሉ የነብሱን ጥሪ እንዲያዳምጥ ጊዜ በመስጠት፤ ለኛም ፍቅርና ተስፋን አቋድሰው ከአድማስ ባሻገር እንድናስብ ሰላደረጉን ባለውለታችን ናቸው ።

በመጨረሻም በዓሉ ግርማ አልሞተም፤ በውስጣችን እየተንቦገቦገ የፀሐይ ብርሃኑን ሲፈነጥቅ ይኖራል !!

ብዕር ለዘላለም ነፃ ሆና ትኑር !!!

በቸር ይግጠመን

ሰኔ 6 ቀን 2002 ዓ.ም. (13/06/2010)

EthioLion.Com